# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

**ቁጥር** 64 ሐምሌ 30 **ቀን** 2001 **ዓ.ም**


የግንቦት 7 ንቅናቄ ደግሞ ደጋግሞ አሳስቧል፡፡ “ብዙሃኑ በድህነት ማዕበል ከመደፈቅ በሚንፈራገጡበት ባህር ውስጥ የጥቂቶች የጥጋብና የድሎት ጀልባ የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር መስመጧ አይቀርም” ብሏል፡፡ “ብዙሃኑ መብታቸው ተረግጦ፣ ፍትህ አጥተው በሚኖሩበት ሃገር፣ የፍትህ መጥፋት የማያሳስባቸው ጥቂቶች የህግ ያለህ የሚሉበት ቀን ሩቅ አይሆንም” ብለናል፡፡

**ከርዕሰ አንቀጽ የተወሰደ**

## የፌደራል ፓሊስ ሙሉ በሙሉ ለማለት በሚቻል ደረጃ በትግራይ ተወላጆች ቁጥጥር ስር መውደቁን የግንቦት 7 ታማኝ ምንጮች አጋለጡ

የፌደራል ፓሊስን የሚመራው ዋና ኮሚቴ አራት አባላት ያሉት ሲሆን ሶስቱ በማያጠራጥር ሁኔታ የትግራይ ተወላጆች ሲሆኑ በኦሮሞ ብሄር ‹‹ኮታ›› እንደተመደበ የሚነገርለት ወርቅነህ ገበየሁም በዘር ሃረጉ ከዚያው የሰሜን ክፍል የተገኘ መሆኑ ታውቋል። በዚህም ምክንያት አራቱም ከአንድ ዘውግ የተገኙ ናቸው፡፡ አራቱ የፌደራል ፓሊስ ዋና ኮሚቴ አባላት ኮሚሽነር ወርቅነህ ገበየሁ፣ በምክትል ኮሚሽነርነት ማዕረግ ሀሰን ሺፋ-፣ ኮማንደር ግርማይ ማንጁስ - የሰው ኃይል እና የምድባ ኃላፊ እና ኮማንደር ተስፋዬ አፍርሶም - የአስተዳደር ጉዳዮች እና የበጀት ኃላፊ ናቸው።

ከዚህም በተጨማሪ በፌደራል ፓሊስ ውስጥ ያሉት መምሪያዎች አሁንም ሙሉ በሙሉ ሊባል በሚችል ደረጃ የትግራይ ተወላጆች ተቆጣጥረውታል።

1. ኮንማደር ታደሰ መሰረት-የምርመራ ማስተባበሪያ ዋና አዛዥ
2. ኮማንደር ሰናይ ገብረ ማርያም -የአድማ ብተና ዋና አዛዥ
3. ኮማንደር ሞኒ ገሰሰ-የጸረ ሽብር ምርመራ ዋና ሀላፊ
4. ኮማንደር ደምሳሽ ሀይሉ-የፌደራል ፓሊስ ቃል አቀባይ
5. ኮማንደር አረፈ አይኔ ሀጎስ-የፌደራል ፓሊስ የመረጃ ሀላፊ እና አዲስ አባበን ከሚቆጣጠሩት 4ት ኮሮች የአንደኛ ሀላፊ
6. ኮማንደር ገብረታቲዮስ-የፌደራል ፓስት እና የጋራዥ ሀላፊ ናቸው።

ከሌላ ብሄር መጥተው የይስሙላ ስልጣን የተሰጣቸው ኢንስፔክተር መሃመድ ገነነ የወንጀል መዝገብ ቤት ኃላፊ፣ ኮሚሽነር በፍቃዱ ቶሌራ የፌደራል ፓሊስ ዳይሬክተር የህግ አማካሪ እና ኮማንደር ኤሊያስ ፊቅይበል የፌደራል ፓሊስ አሻራ እና ትንተና ኃላፊ ብቻ መሆናቸው ታውቋል። **ወደ ገጽ 2 ዞሯል**

የግንቦት 7 ንቅናቄ ጥሪ፣ ሁላችንም ይህ ጎደላት በማንላት የኢትዮጵያ ውስጥ በዜግነታችን ኮርተን፣ ሁሉም አይነት ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቻችን ተከብረው ተፋቅረን/ ተዋደን የምንኖርባት ሃገር በቅርቡ ለማየት በጋራ ለትግል እንድንነሳ ነው።

**አንዳርጋቸው ጽጌ**

## በፓሪስ የስፖርት ፌስቲቫል ግንቦት 7 የተሳኩ ዓላማን የማስተዋወቅና ገቢ ለማሰባሰብ ሥራዎችን ከወነ

በፈረንሳይ ዋና ከተማ ፓሪስ በተደረገው ዓመታዊ የስፖርት ፌስትቫል ላይ የግንቦት 7 አባላት ንቅናቄውን ለኢትዮጵያውያን በማስተዋወቅና የገቢ ማሰባሰብ ስራ በመስራት ጥሩ ውጤት ለማግኘት ችለዋል።

በፌስቲቫሉ ወቅት የግንቦት 7 ዓላማዎችን የሚገልጹ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ በራሪ ወረቀቶች የተበተኑ ሲሆን የግንቦት 7ትን አርማና የተለያዩ አርበኞችን ምስሎች የያዙ ቲሸርቶችም ለሽያጭ ቀርበው ነበር።

የግንቦት 7 አባላት የተለያዩ የፖለቲካ መስመሮችን ከሚከተሉ ኢትዮጵያውያን ጋር በግልና በቡድን ውይይቶችን ያደረጉ ሲሆን፣ በርካታ ኢትዮጵያውያንም ለንቅናቄው ያላቸውን ድጋፍ በተለያዩ መንገዶች ሲገልጹ ተስተውሏል። አንዳንዶች ግንቦት 7 ከተቋቋመ ጊዜ አንፃር ሲታይ እያሳየ ያለው እንቅስቃሴ እንዳረካቸውና የኢትዮጵያ ትንሳኤ እየተቃረበ እንደመጣ እየተሰማቸው መሆኑን ገልጸዋል። **ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

ግዜ
ግንቦት 7 ዜና

## የህሊና እስረኛዋ ወ/ሮ እማዋይሽ አለሙ በወያኔ ወህኒ እና መርማሪ ፖሊሶች እንግልት ደረሰባቸው

ከእነ ብርጋዴር ጄኔራል ተፈራ ማሞ ጋር በማበር ‹‹መንግሥቴን ሊገለብጡብኝ ነበር›› ብሎ ወያኔ አስሮ እያገላታቸው ካሉት በርካታ ወገኖቻችን ውስጥ አንዷና በዚያ መዝገብ ውስጥ ከተከሰሱት ውስጥ ብቸናዋ ሴት የሆኑት ወ/ሮ እማዋይሽ አለሙ በወያኔ ፓሊሶችና ሰላዬች እንግልት እየደረሰባቸው መሆኑን ከወህኒ ቤቶች ያገኘናቸው መረጃዎች አረጋገጡ።

የሴቶች የነፃነት ትግሉን መቀላልና አመራርም ላይ መገኘት ያስደነገጠው ወያኔ ሴት እስረኞች ላይ አረመኔነቱ እንደሚከፋ ምንጮቻችን ያስረዳሉ፡፡ ‹‹ሴት እስረኞች ጨለማ ቤት ውስጥ ይዘጋባቸዋል፤ ‹‹ማድ ቤት ብትከተቺ ኖሮ እዚህ ችግር ውስጥ ባልገባሽም ነበር›› ከማለት ጀምሮ ለመስማት የሚሰቀጥጡ የሴትን ክብር የሚነኩ ስድቦችን ይሰደባሉ፤ አስነዋሪ መጎነታተሎች ይፈጸማሉ፤ ለሴቶች ጤንነት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን በመንፈግም ችግር ውስጥ እንዲገቡ ይደረጋሉ›› ሲሉ ውስጥ አዋቂዎች ለአዲስ አበባ ዘጋቢዓችን ገልፀዋል። ይሁን እንጂ ይህ ሁሉ ወከባ እየተደረገባቸውም ቢሆን የሴት ታጋዮቻችን የመንፈስ ጽናት አስገራሚ እንደሆነ መረጃ ሰጪዎቻችን ይገልፃሉ፡፡ **ወደ ገጽ 2 ዞሯል**

## ወያኔ 15 አሜሪካዊያን የእንግሊዘኛ ቋንቋ አስተማሪዎችን ከአገር አባረረ

ከአዲሱ የአሜሪካ አስተዳደር ጋር ሆድና ጀርባ እየሆነ የመጣው የመለስ አገዛዝ 15 አሜሪካዊያን የእንግሊዘኛ ቋንቋ አስተማሪዎችን ከአገር ማባረሩን የአሜሪካ ድምጽ ዜና አገልግሎት ወይም ቪ’ኦ’ኤ ዘገበ። እርምጃው የወያኔ ቁንጮዎች የደረሱበትን ተስፋ መቁረጥ ደረጃ አመልካች ነው ሲሉ የፖለቲካ ተንታኞች ተናገሩ።

በኦሮሞያ ክልል ምስራቅ ሀረርጌ ለበርካታ ሳምንታት የእንግሊዘኛ ቋንቋን ለአካባቢው ህዝብ ሲያስተምሩ የነበሩ አስራ አምስት አሜሪካዊያን ተማሪዎችን ማባረሩን የአሜሪካ ድምጽ ዘገበ። የአጋዴን ብሄራዊ ነጻ አውጪ ግንባር እና ወያኔ ከሚዋጉበት አካባቢ አቅራቢያ ባሉ የገጠር ከተሞች ያስተምሩ የነበሩትን አሜሪካውያን ወያኔ በተመሳሳይ ሰአት ሀሮ ማያ፤ አወዳይ፤ ጎቦ እና ዳድር በሚባሉ አካባቢዎች ያረፉባቸውን ቤቶች በመበርበር የሞባይል ስልኮቻቸው እና ካሜራዎቻቸው ተቀምተው ለአንድ ቀን ሙሉ ቃላቸውን እንዲሰጡ የተደረጉ ሲሆን ወደ አዲስ አበባ ለተጨማሪ ምርመራ መላካቸው ተገልጿል። ቪኦኤ ምንጮቹን ጠቅሶ እንደዘገበው ፓሊስ አሜሪካኖቹን ፎቶግራፍ በማንሳት፤ ነዋሪዎችን ስለ ምርጫ 97 እና ስለ መጪው ምርጫ ጠይቃችኋል፤ ቪዛችሁ አግባብነት የለውም የሚል ምክንያቶችን እየደረደረ ሲያወግዛቸው ነበር።

ቋንቋ ለማስተማር በበጎ ፈቃደኝነት የመጡት አሜሪካዊያን ተማሪዎች በእስር በቆዩባቸው ሁለት ቀናት ቤተሰባቸውንም ሆነ የአሜሪካ ኤምባሲን እንዲያገኙ እንዳልተፈቀደላቸው ታውቋል። **ወደ ገጽ 3 ዞሯል**

## መለስ ዜናዊ ስልጣን እሊቃለሁ እያለ በዙሪያው ያሰባሰባቸውን አሻንጉሊቶች እያስፈራራ ጎን ለጎን በ30 ሚልዮን ዘመናዊ የመኖሪያ ህንጻ በሚንልክ ቤተመንግስት ለማሳነጽ በጄት ደተጠየቀ

ለዘረኛው አምባገነን መለስ ዜናዊ መኖሪያ ቤት ግንባታ ከሰላሳ ሚሊዮን ብር በላይ የቤተመንግሰት አስተዳደር መጠየቁን ሳምንታዊ የእንግሊዘኛ ጋዜጣ ፎርቹን ዘገበ። እንደ ጋዜጣው ዘገባ ሚኒልክ ቤተመንግስት ውስጥ የሚሰራው የመለስ ዜናዊ ቤት ባለአምስት ፎቅ ሲሆን የተለያዩ የእንግዳ መቀባያዎችም ይኖሩታል። የሚሰራው ፎቅ እጅግ ዘመናዊ እና በቅንጦት እቃዎች እንደሚሞላ ተገልጿል። በቅርቡ ስራው እንደሚጀመር የሚጠበቀውን ህንጻ ዲዛይኑን እና የግንባታ ስራው ብሄራዊ አማካሪዎች ለተባለ ኩባንያ መሰጠቱ ታውቋል። ከመንግስት መስሪያ ቤቶች በተለየ ሁኔታ ውዝፍ እዳዎችን ባለመክፈል እና በከፍተኛ ደረጃ ንብረት በማባከን የሚታወቀው የቤተ መንግስት አስተዳደር ጠይቅ የተባለውን ግዙፍ መጠን ያለው ብር ለይስሙላ ያከል ጠይቋል።

**ወደ ገጽ 3 ዞሯል**

## ወያኔን በማስወገድ በከተሞች የተንሰራፋውን ዘረፋ እናስቁም

ኢትዮጵያ ቀምቶ ከመብላት በረሃብ መሞት የሚመረጥባት አገር ናት። በችጋር ምክንያት ገበሬው ቀዬውን ለቆ ወደ ከተማ በተሰደደባቸው ጊዜዓት ከተሜውን ወገኑን አስተዛዝኖ ለመነ እንጂ ዘርፎ ልብላ አላለም። ድህነት ወንጀል ሆኖ በረሃብ ምክንያት የተሰደደውን ወገናችን ታፍሶ ከከተማ ውጭ እንዲታጎር በተደረገ ጊዜም ለዚህ ግፍ የሰጠው ምላሽ በአጠገቡ ያገኘውን የሰው ንብረት መዝረፍ አልነበረም።

በ1983 ዓም የመከላኪያ ሠራዊት በተበተነበት ወቅት የሠራዊቱ አባላት ያሳዩት ጨዋነት ከኢትዮጵያዊያን ህሊና የሚጠፋ አይደለም። በርካታ የተበተነው ሠራዊቱ አባላት መሣሪያ ተሸክመው ወርቅ ቤት በራፍ ቆመው ‹‹አገሬ መግቢያ መሳፈሪያ ሙሉልኝ›› እያሉ ወገናቸውን መለመናቸው ዛሬ ላይ ሆነን ስናስበው በእጅጉ መደነቃችን አይቀርም።

አሁን ይኸ ሁሉ ተቀይሯል። ዛሬ ዘራፊው ራሱ መንግሥት ሆኖ ስለላውን፣ ፓሊሱን፣ ፍርድ ቤቶችንም ያዛል። ወያኔ ውስብስብ ከሆነው ኤፈርት-መር ሙስና እስከ ተራ የመንደር ማጅራት መቺነት በሁሉም የዘረፋ ዓይነቶች እንደተሰማራ የማያጠራጥሩ መረጃዎች አሉን። የከተማ ነዋሪው ስጋት ውስጥ ገብቶ እንዲኖር በታደቀ ሁኔታ ሽብር የሚፈጥሩ ቦዘኔዎችን በከተሞች ውስጥ አሰራጭቷል።

“እከሌ ባልታወቁ ሰዎች ተደበደበ” “እከሌ የደረሰበት አልታወቀም” “አከሊት ደግሞ ባልታወቁ ሰዎች ታፍና ህሊናዋን ስታ መንገድ ዳር ወድቃ ተገኘች” የሚሉ ዜናዎች በመለመዳቸው ምክንያት ዜና መሆናቸው እየቀረ ነው። በተለይ ወጣት የተቃዋሚ ፓርቲ ደጋፊዎችና ጋዜጠኞች “ባልታወቁ ሰዎች” የመደብደብና የመታፈን ዋነኛ ሰለባዎች ናቸው። በአሁኑ ሰዓት ከወያኔና ወዳጆቹ ጋር መለስተኛ ቅራኔ ውስጥ የገባ ማንኛውም አካል በማጅራት መቺዎች ከመደብደብ እንደማያመልጥ በቅርቡ በኦርቶዶክስ ቤተክህነት ጳጳሳት ላይ የደረሰውን ማስታወስ ይበቃል።

ተራ ሌቦችም በወያኔ ተግባር ተበረታተዋል። የወያኔ የዘረፋ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ፖሊሲዎች ወያኔዎችንና ጥቂት አጫፋሪዎቻቸውን ሚሊየነር ቢያደርጉም ድሃውን ግን የባሰ አደህይተዋል፤ አዳዲስ ድሆችንም በብዛት ፈጥረዋል፡፡ የወያኔ ፓሊሲዎች ራሳቸውን ችለው የማስተዳደር ተስፋቸው የተሟጠጠ፤ ከዘረፋ ውጭ ህይወታቸውን ማቆያ የማይታያቸው በብዙ ሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ጎልማሶችን ፈጥሯል፡፡ እነሱም ሲሻቸው በራሳቸው የጎበዝ አለቃዎች እየተመሩ፤ ወያኔ ሲሻው ደግሞ በራሱ ሰላዮች የጎበዝ አለቃነት እየመራቸው ከተሞችን ያምሳሉ፤ ህዝብን ያሸብራሉ። በተለይ አዲስ አባባ ውስጥ አመሻሽቶ በሰላም እመኖሪያ መመለስ እያስቸገረ ነው። ልጃገረዶች የማታ ትምህርት ቤት አምሽተው በሰላም ወደቤታቸው መግባት ተቸግረዋል። እናቶች መቀነታቸው እየተፈታ በመከራ የቋጠሯትን ይነጠቃሉ። ከተሞቻችን “ጉልበተኛው ደካማውን ዘርፎ ይብላ” የሚል ህገ-አራዊት ታውጆባቸዋል።

ይህ ሁኔታ በአጠቃላይ የወያኔ ሥርዓት ምን ያህል የነቀዘ መሆኑን ቁልጭ አድርጎ ያሳያል ብለን እናምናለን። ይህ ንቅዘት በአገራችንና በባህላችን ላይ ከዚህ የከፋ ውድመት ከማድረሱ በፊት አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ እንዳለብን ያስገነዝበናል። ችግሩን ከመሠረቱ የሚፈታው እርምጃ ደግሞ ወያኔ ተወግዶ በምትኩ በሕዝብ የተመረጠ መንግሥት እንዲኖር ማድረግ ነው።

ይህ ወቅት አገርን ከጥፋት ማዳኛ እንጂ የረዥም ጊዜ ኢንቨስትመንት የሚታሰብበት ጊዜ አይደለም። በአሁኑ ሰዓት በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ውስጥ ኢንቨስት የሚያደርግ አንድም ሁኔታውን ያልተደረዳ የዋህ፤ አሊያም ራሱ የወያኔ ጭፍራ የሆነ ዘራፊ መሆን አለበት። በአሁኑ ሰዓት ለምንም ዓይነት ነፃ ኢንቬስትመንት ዋስትና የለም። ወያኔ ወይ መንግሥት ሆኖ አሊያም ተራ የመንደር ዘራፊ ሆኖ ነፃው ኢንቨስተር ለዓመታት ለፍቶ ያጠራቀመውን በአንዲት ጀንበር ይዘርፈዋል። ዛሬ ሕዝብ የኑሮ ዋስትና ያጣበት ወቅት ነው። ዛሬ ንግድ ዋስትና ያጣበት ወቅት ነው። ሌላው ቢቀር የእምነት ተቋማት እንኳን ዋስትና አጥተዋል።

የግንቦት 7 ንቅናቄ ደግሞ ደጋግሞ አሳስቧል፡፡ “ብዙሃኑ በድህነት ማዕበል ከመደፈቅ በሚንፈራገጡበት ባህር ውስጥ የጥቂቶች የጥጋብና የድሎት ጀልባ የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር መስመጧ አይቀርም” ብሏል፡፡ “ብዙሃኑ መብታቸው ተረግጦ፣ ፍትህ አጥተው በሚኖሩበት ሃገር፣ የፍትህ መጥፋት የማያሳስባቸው ጥቂቶች የህግ ያለህ የሚሉበት ቀን ሩቅ አይሆንም” ብለናል፡፡ “እኔ ሆዴን ከሞላሁ፣ አጥሬን መሳሪያ በታጠቁ ዘበኞች 24 ሰአት ካስጠበቅሁ፤ እኔ ከባለስልጣናቱ ጋር ተስማምቼ በሽርክና እስከከበርሁ፣ ስሌላው መራብ፣ ስለሌላው ሰላምና ፍትህ ማጣት ምን አገባኝ የሚል የዛሬ የግዴለሽነት ኢንቨስትመንት ነገ ትርፉ ለቅሶና ዋይታ ነው” ብለናል፡፡ ዛሬም ይህንኑ ደግመን ደጋግመን እናሳስባለን፡፡ ስለዚህም ነው ይህን እየተስፋፋ ያለ የዘረፋና የሌብነት ባህል የሁላችንንም ህይወት ወደ ምድራዊ ሲኦል ሳይቀይረው በፊት ትኩረት ሰጥተን ለመፍትሄው በጋራ እንትጋ የምንለው፡፡

ወያኔ ካልተወገደ በስተቀር ዘረፋ ህጋዊ ይደረጋል እንጂ ሊቆም አይችልም። የወያኔ ኢኮኖሚ ምንጩ ዘረፋ በመሆኑ ቀስ በቀስ ዘረፋን ህጋዊ እያደረገ ነው። “የፀረ-ሽብርተኝነት ህግም” አንዱ ዓላማው ዘረፋን ህጋዊ ማድረግ ነው። የአንድን ኢንቬስተር ሃብት ለመውረስ በሽብርተኝነት ደጋፊነት በአንድ ፓሊስ መጠርጠር በቂ ነው። ዘረፋን ለማጥፋት ወያኔን ማስወገድ የግድ ነው። ይህ ደግሞ ፋታ ሊሰጠው የሚገባው ተግባር አይደለም። ባህላችንና የኑሮዓችን መሠረቶች እየተናጉ ነው። ወያኔን በማስወገድ በከተሞች የተንሰራፋውን ዘረፋ እናስቁም፡፡

### የፌደራል ፓሊስን የሚመራው . . . ከገጽ 1 የዞረ

እንደ ወያኔ ጦር ሠራዊት ጀኔራሎች ሁሉ የፌደራል ፓሊስ ሹማምንትም በሙስና የተዘፈቁ፤ ድሃውን ህዝብ በጥይት የሚቆሉ ብቻ ሳይሆን በቁም የሚመዘብሩ ዘራፊዎች መሆናቸውን ግንቦት 7 እያሰባሰበ ያለው መረጃ ያመለክታል። ወደፊት እነዚህን ዘራፊ የፓሊስ መኮንኖች ያጋበሱትን ንብረት ዝርዝር ለሕዝብ ይፋ እናደርጋለን።

የአዲስ አበባ ፓሊስም በወያኔ መረን የለቀቀ ዘረኝነት መተብተቡ ይታወቃል። ወደፊት የአዲስ አበባ ፓሊስ ከፍተኛ ሹማምንትን የብሄር ተዋጽዖ ለሕዝብ ይፋ እንደርጋለን።

### የህሊና እስረኛዋ ወ/ሮ እማዋይሽ አለሙ . . . ከገጽ 1 የዞረ

“በወ/ሮ እማዋይሽ አለሙና ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ላይ እየታየ ያለው ጽናት አሳሪዎቻቸውን ሳይቀር አስገርሟል” ይላሉ ምንጮቻችን።

በዚህ ጉዳይ ላይ አስተያየት የአዲስ አበባው ዘጋቢያችን ያነጋገራቸው አንድ የእድሜ ባለፀጋ ‹‹በፋሺስት ጣሊያን ወረራ ወቅት ለኢትዮጵያ ነፃነትና ክብር የተዋደቁ ስመ-ጥር ሴት አርበኞች ነበሩ›› በማለት የቀድሞ አኩሪ ታሪካችንን ካስታወሱ በኋላ “ዛሬም በተመሳሳይ ሁኔታ እንደ ወ/ት ብርቱካን እና ወ/ሮ እማዋይሽ ዓይነቱ ጀግኖች ከወያኔ ዘረኛና አረመኔ ሥርዓት ጋር ፊት በፊት በመጋፈጥ መስዋዕትነት በመክፈል ላይ መሆናችቸው ሁላችንንም - ወንዶችንም ሴቶችንም - የሚያነቃቃ ነው” ብለዋል።

የመረጃ ምንጮቻችን ወያኔ በወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ እና ወ/ሮ እማዋይሽን የሚያደርሰው ተከታታይ የሆነ የስነልቦናዊና አካላዊ ሰቆቃ እየተከታተሉ ለግንቦት 7 ዘጋቢያችን እንደሚያሳውቁ ቃል ገብተዋል።

በግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን

የፖስታሳጥን ቁጥር :- POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

# ከወያኔ ዘረኛ እምነቶችና ድርጊቶች ምን እየተማርን ነው። የዘረኛነትን አደጋ ለመታገል ምን ማድረግ እንችላለን?

አንዳርጋቸው ጽጌ (ሐምሌ 5 ቀን 2001 ዓም፣ ሚነሶታ አሜሪካ በግንቦት 7 ህዝባዊ ስብሰባ ላይ የቀረበ ንግግር) ካለፈው የቀጠለ

ሌላው ትልቁ ቁምነገር የወያኔን ዘረኛነት ለመታገል ሁሉም የዘረኛነት ግንብ የሚገነባ ከሆነ፣ ዘረኛ ጦሩን የሚስል ከሆነ፤ በዘረኛ መንገድ ወታደራዊ ጉልበቱንና ሃብቱን አስቀድሞ ያደራጃውን ወያኔን ታግሎ የማስወገድ እድሉ ጠባብ እንደሚሆን ነው። ትግሉ ወያኔ ላይ ብቻ ያነጣጠረ ሳይሆን በየራሱ ዘር ተደራጅቶ ሊያጠቃኝ ይችላል ከሚል ሌላም ዘር ጋር ጭምር መሆኑ አይቀርምና። ከእዚህም አልፎ በአንድ አጋጣሚም ይህ ወያኔን የመጣል የተለያዩ ድርጅቶች የተናጠል ትግል ቢሳካ መጨረሻው የወያኔን ዘረኛ ስርአት በሌላ ዘረኛ ስርአት መተካት ይሆናል። የእዚህ ውጤት ደግሞ ማለቂያ የሌለው የዘር ፍጥጫ፣ ግጭት ማቀጣጠል ይሆናል። ይህ የሚያስገነዝበን ዘረኛውን ወያኔን ታግለን ለማሸነፍ፤ አሸንፈንም ሁሉም የሃገሪቱ ዜጎች ያለምን መድለዎ በሰላምና በእርጋታ መኖር የሚችሉበትን ሁኔታ መፍጠር የምንችለው ገና ካሁኑ ዘረኛነትን የዘለለ የፖለቲካ ንድፈሃሳብና አደረጃጀት የሚያስፈልገን መሆኑን ተገንዝበን ይህንንም እውን ለማድረግ ተግተን ከሰራን ብቻ ነው።

ቀደም ብዬ እንደጠቀስኩት የወያኔ ዘረኛነት መነሻው ፍትሃዊ የሆነውን የብሄረሰቦች/ የዘውግ ማህበረሰቦች የመብት ጥያቄ በዋንኛነት ከሚመለከታቸው የሃገሪቱ ዜጎች ቀምቶ፤ እነዚህን የመብትና የእኩልነት ጥያቄዎች ወያኔ ሊገነባው ላሰበው ዘረኛ ስርአት መሳሪያዎች ስላደረጋቸው ነው። ወያኔ ይህን ማድርግ የቻለው የዘውግ ስሜት ሃገራዊ የሆነውን የዜግነት ስሜት በፕሮፓጋንዳም ይሁን በአደረጃጀት ደረጃ እንዲረግጠው ማድረግ በመቻሉ ነው። እኛም ስለፈቀድልነት ነው። በሃገራችን ሁላችንም ፍትሃዊነቱን የምንቀበለው የዘውግ እኩልነት ጥያቄ አንድ አይነት ሃገራዊ መጠብቅ ካልተደረገለት በቀላሉ ራሱን ወደ እኛ እና እነሱ ወደሚሉ ዘረኛ ክፍፍሎች የሚወስድ መሆኑን ካለፉት 18 አመታት ታሪካችን የተማርነው ነው። ደጋግሞ ደጋግሞ እንደታየውም የዘውግ የእኩልነት ጥያቄን ከሃገሪቱ ዜጎች በሙሉ የዜግነት መብት ጥያቄ ጋር ሳያስተሳስሩ ሰዎችን አጥንትና ደማቸውን እየመነዘሩ የሚያሰባስቡ ድርጅቶች ውለው አድረው የሚያጠናክሩት ዘረኛነትን ብቻ ነው።

ይህን አደጋ መጠቆም ፍትሃዊ የሆነው የዘውግ እኩልነት ዴሞክራሲያዊ ጥያቄዎችን እንርሳ፣ እንደሌሉ አድርግን እንቁጠራቸው ማለት አይደለም። የዘውግ/ የብሄር/ብሄረሰብ የእኩልነት ጥያቄዎችን ዘረኛ አመለካከትንና አደረጃጀትን ሳናጠናከር ምላሽ የምንሰጥበትን ሁኔታ እንፍጠር ለማለት ብቻ ነው። ይህን ማድረግ የምንችለው የሁሉንም የሃገሪቱን ዜጎች፤ በየትኛውም የሃገሪቱ ክፍል ይኑሩ፣ ሁሉም በዜግነታቸው የሚገቧቸውና ሊገሰሱ የማይችሉ መብቶች በማስቀመጥ ብቻ ነው። በእዚህ መብቶች መከበር ዙሪያ ሁሉም ዜጎች በጋራ ታግለው፣ በዜግነታቸው የሚኮሩበት ሃገራዊ የፖለቲካ ስርአት መፍጠር የዘረኛነትን አደጋ መከላከያው ቁልፍ መሳሪያ ነው።

የዘውግ እኩልነት ፍትሃዊ ጥያቄ በሃገር ውሰጥ ዜጎች መብታቸው በመከበሩ የተከበረ መብት መሆኑን ማረጋገጥ ስንችል በዘውግ ማንነታችንና በአንድ ሃገር ዜግነታችን መሃከል ያለው ቅራኔ ይጠፋል። ወያኔ እንደሚለው የአንድ ሃገር ዜግነታችንና የአንድ ዘውጌ ማህበረሰብ አባልነታችን በተፎካካሪነት ወይም በእኩልነት የምናስቀምጥበት ሁኔታ ከተፈጠረ ግን በእነዚህ ሁለት ስሜቶች ማሃከል የሚፈጠረው መሳሳብ ለሁላችንም የጋራ የሆነች ሃገር በመፍጠሩ ስራችን ላይ ትልቅ አደጋ የሚያስከትል መሆኑን መረዳት ይኖርብናል። የዘውግ መብቴን የማታከብር ኢትዮጵያ ትበጣጠስ የሚል የዘውግ አባል በተበጣጠሰች ኢትዮጵያ ወስጥ ሰላምና እርጋታ አግኝቶ የራሱን ሃገር ፈጥሮ የዘውግ መብቱን ማስከበር የሚችልበት ሁኔታ እውን ሊመጣ ይችላል ወይ ብሎ ሊጠይቅ ይገባዋል። በበኩሌ ይህ ሁኔታ ሲፈጠር ማየት ስለማልችል የዘውግ መብት እንዲከበር የሚታገሉ ሁሉ ጠንካራና ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን መገንባትም የእዚሁ ትግላቸው ዋንኛው አካል አድርገው ሊያዩትና ሃላፊነትም ወስደው ሊዋደቁለት የሚገባ ጉዳይ ነው የሚል እምንት አለኝ። ሃገራዊ ፖለቲካ የሚያስተሳስራቸው፣ ለሃገራዊ ዴሞክራሲዊና ፍትሃዊ ተቋማት መኖር በጋራ የሚታገሉ የአንድ ሃገር ዜጎች ከሌሉ፤ ሁሉም የዘውግ ማንነቱን ከዜግነቱ አስቀድሞ የሚቆምበት ሁኔታ ከተፈጠረ የዘረኛነትን ሽርተቴ ማስቆም እንደማንችል ማወቅ ይኖርብናል።

ወያኔ አስካሁን ከነብልግናው በሁላችንም ጫንቃ ላይ መሰንበት የቻለው፣ ሌሎች ዘውጌ ማህበረሰቦችን በተለይ ትልልቆቹን የሃገሪቱን ዘውጌ ማህበረሰባት፤ በዘውግ ፖለቲካ አጥንት ንክሻ ላይ ብቻ እንዲረባረቡ ማድረግ በመቻሉ ነው። ወያኔ ግን የፌደራል አገዛዙን ሃብት፣ ጉልበት ጠቅልሎ የያዘበት፣ የሃገሪቱን የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ለራሱ ዘረኛ የስልጣን እድሜ ማራዘሚያ አድርጎ መቅረጽ በመቻሉ ነው።

ከእዚህ የምንወስደው ትምህርት ግልጽ ነው። ሁላችንም፤ አስከዛሬ ድረስ በራሳቸው የዘውግ ፖለቲካ አጀንዳዎች ዙሪያ ሲሽከረከሩ የነበሩ ግለሰቦችና ቡድኖችን ጨምሮ፣ ሃገራዊ ለሆነው የፖለቲካ ምህዳር ትኩረት መስጠት፤ የወያኔ ኋላቀር አመለካከትና ድርጊት ወደ ነበረበት የታሪክ ቆሻሻ መመለሻው ቁልፍ መሳሪያ መሆኑን ነው።

በተለይ ራሳቸውን በዘውግ የአደራጁ ቡድኖች የዘውጋቸውን አበላት ብቻ ሳይሆን ሁሉንም ዜጎች የሚመለከቱ ሃገራዊ አጀንዳዎችን ማንሳት፣ በሃገር ደረጃ የሚፈጠረውን የፖለቲካ ስርአት ቅርጽ መስጠት፣ አልፎ ተርፎም ሃገራዊ ትግሉን የመምራታ ሃላፊነትና ግዴታ አለባቸው። ይህንን ለማድረግ ችሎታው ብቃቱና ሰፊ ህዝባዊ መሰረት እንዳላቸው በፍጥነት ተረድተው ቢንቀሳቀሱ የራሳቸውን የዘውግ አበላት ብቻ ሳይሆን የተቀረውንም ኢትዮጵያዊ ወገናቸውን የመከራ ቀን በማሳጠር የሚጫወቱት ወሳኝ ሚና ይኖራል የሚል እምነት አለኝ።

የጸረ ወያኔ ትግላችን እንዲሳካ፤ የሃገራችን በርካታ ትውልዶች የዜግነትና የዘውግ እኩልነት መብቶቻቸው እንዲከበሩ የከፈሉት ማለቂያ የሌለው መስወአትነት ውጤት እንዲፈራ፣ ከድህነት ከስደት መላቀቅ ከፈለግን ወያኔ በሃገራችን ፖለቲካ ውስጥ የፈጠራቸውን በተለይ ከዘር ጋር የተያያዙ አዳዲስ ተግዳረቶች challenges/ የሚመጥን የፖለቲካ አመለካከትና የአደረጃጀት ለውጥ ማድርግ ይኖርብናል።

የዘመኑን የፖለቲካ ፈተና ተግዳሮት/challenge በነባሩ የፖለቲካ አመለካከትና አደረጃጀት እስርቤቶች ውስጥ ሆነን ልናልፈው አንችልም። የኔ ተስፋ ይህ ግንዛቤ በሁላችንም ውስጥ በፍጥነት ተጭሮ በጋራ ትግል የወያኔን ዘረኛ አምባገነናዊ ስርአት በሃጋራችን የመጨረሻው አምባገነናዊ አገዛዝ ለማድረግ የምንችልበት የትግል ምእራፍ በፍጥነት ሲጀምር ማየት ነው። ይህ ተስፋ ብቻ ሳይሆን ተጨባጭ የሆነ ድርጊት ሊሆን እንደሚችል አመላካች ነገሮች ይታዩኛል።

የግንቦት 7 ንቅናቄ ጥሪ፣ ሁላችንም ይህ ጎደላት በማንላት የኢትዮጵያ ውስጥ በዜግነታችን ኮርተን፣ ሁሉም አይነት ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቻችን ተከብረው ተፋቅረን/ተዋደን የምንኖርባት ሃገር በቅርቡ ለማየት በጋራ ለትግል እንድንነሳ ነው። ይህን በማድረግ ሩስያዊው ዶስቶቭስኪ ካስጠነቀቀን ገሃነብ ራሳችንንና መጪውን ትውልድ ለማዳን በጋራ በወያኔ ላይ እንድንነሳ ነው።

አመሰግናለሁ

አንዳርጋቸው ጽጌ

## ወያኔ 15 አሜሪካዊያን . . . ከገጽ 1 የዞረ

ከገጽ 1 የዞረ

የኤምባሲው ባለስልጣኖች ተማሪዎቹ በፓሊስ ታጅበው አውሮፕላን ሊሳፈሩ ሲሉ ለአጭር ደቂቃ ከማየታቸው ውጪ ማግኘት ያልቻሉ ሲሆን አንድ ተማሪ በተለየ ሁኔታ ለተጨማሪ ቀናት ለብቻው ታስሮ እንደነበረ ተገልጿል።
የአሜሪካ ኤምባሲ ቃል አቀባይ መንግስት እስሩን ያካሄደበትን ሁኔታ እና ኤምባሲው ከዜጎቹ ጋር እንዳይገናኝ መከልከሉ ከፍተኛ ጥያቄ እንዳጫረባቸው ተናግረዋል።

ሽመልስ ከማል ለአሜሪካ ድምጹ የአማርኛ ዘጋቢ እስክንድር ፍሬው "ተማሪዎቹ ከመጡበት ተልእኮ ውጪ"ተሰማርተው ተገኝተው ነበር ከማለቱ ውጪ የትኛውንም ህግ ተላለፋችሁ ተብለው እንዳልተከሰሱ ታውቋል።

በሆነ ባልሆነ ምክንያት ኢትዮጵያውያን ዜጎችን የሚከስ እና የሚገድለው ወያኔ፥ በአሜሪካኖቹ ላይ ይህን ተግባር መፈጸሙ ከኦባማ አስተዳደር ጋር ግንኙነቱ እየተበላሸ ስለመጣ በተስፋ መቁረጥ ስሜት ሆኖ ሊሆን ይችላል የሚሉት ታዛቢዎች፤ የተማሪዎቹ መታሰር ከዚህም ያለፈ አንድምታ ሊኖረው እንደሚችል ተናግረዋል። መለስ በኦጋዴን ህዝብ ላይ የፈጸመው የጦር ወንጀል እና የዘር ፍጅትን የሚያጋልጡ ማናቸውም መረጃዎችን የማፈን ጽኑ ፍላጎት አለው፤ በአካባቢው ማንኛውም የውጪ ድርጅት እንዳይገባ ካገደበት አንደኛው እና ዋነኛውም ምክንያት የሚፈጽመው ወንጀል እንዳልይጋለጥ ስለሚፈራ ሊሆን እንደሚችል ጠቁመዋል። ነገር ግን መለስ የፈለገውን መረጃ ለማፈን ቢሞክር በተራቀቀ ቴክኖሎጅ በሳተላይት የተሰበሰቡትን ምስሎች ጨምሮ ግፉን የሚያሳይ በቂ መረጃ ስላለ ከተጠያቂነት አይድንም ብለዋል።

## መለስ ዜናዊ ስልጣን እለቃለሁ እያለ . . . ከገጽ 1 የዞረ

ከ50 ሺህ በላይ ጎዳና ተዳዳሪዎች ባሉባት ከተማ እና በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ረሀብተኞች ባሉባት አገር ለአንድ ዘረኛ አምባገነን መኖሪያ ያን ያህል ገንዘብ ለማፍሰስ መዘጋጀት ወያኔ የደረሰበትን የዝቅጠት ጫፍ አመላካች ነው ተብሏል።
ይህ በእንዲህ እንዳለ መለስ ዜናዊ በድርጅቱ ውስጥ ባሉ አመራሮች በኩል "መለስ ከስልጣን መልቀቅ የለበትም። ማንኛውንም ዘዴ ተጠቅመን በስልጣን እንዲቆይ እንደርገዋለን" የሚል እና ለዚህም ድጋፍ የሚያሰባስብ ኮሚቴ አዋቅሯል።
እንደ ፎርቹን ዘገባም በመቶ ሺህዎች፣ ምናልባትም አንድ ሚሊዮን፣ የሚሆኑ ፊርማዎች መለስ ከስልጣን አይውረድ የሚለውን ሃሳብ በመደገፍ ተሰብስበዋል።

"በአለም አቀፍ የሰብአዊ መብት እና የዘረ ፍጅት ተከላካይ ተቋማት ክስ የሚቀርብበት መለስ ዜናዊ እራሱን እና ጀሌዎቹን ካልሆነ በቀር ይህ ለመድረክ ሊያበቃ የሚያሰባስበው የፊርማ ተውኔት ማንንም እንደማያሳምን ግልጽ ነው" ሲሉ በዚህ ጉዳይ ላይ ያነጋገርናቸው አስተያየት ሰጪ ተናግረዋል።

## በአዲስ አበባ የዝርፊያ መባባስ የወያኔ ከተማዋን መምራት አለመቻል ያመለክታል ተባለ

በአዲስ አበባ ከተማ የዝርፊያ ወንጀሎች እየተባባሱና ዓይነታቸውም እየተቀየረ መምጣቱ ከአዲስ አበባ ፓሊስ የተገኙ መረጃዎች ያመለክታሉ። ዘራፊዎች የፓሊስ ወይም የወታደር ዩኑፎርሞችን የለበሱና መሣሪያም የታጠቅ በመሆናቸው ዘራፊዎቹ የፓሊስ ልብስ ይልበሱ ወይም ፓሊሶች ወደ ዘራፊነት ይቀየሩ መለየት ለነዋሪው የሚቻል አይደለም። አቶ አለማየሁ የተባሉ የአዲስ አበባ ነዋሪ "ፓሊስና ሌባው መለየት ስልማልችል፤ ፓሊስ ባየሁ ቁጥር እጠነቀቃለሁ" ብለዋል። በዚህ ጉዳይ ላይ አስተያየታቸውን እንዲሰጡን የጠየቅናቸው ተንታኝ "አዲስ አበባ ከሌሎች የአፍሪካ ከተሞች የምትለይበት ባህርይ የወንጀሎች አነስተኝነት ነበር። ጎብኚዎች ያለአንዳች ጥበቃ የሚነግዱ የወርቅ ቤቶችንና ሥጋ ቤቶችን እያዩ ማመን ይቸገራሉ። ይህ ግን የሆነው በፓሊስ ጥበቃ ብርታት ሳይሆን በማኅበረሰቡ የሰፈነውን የሰውን ንብረት ያለመንካት ባህል ነው፡፡ ወያኔ አዲስ አበባ ከመግባቱ አስቀድሞ ማዕከላዊ መንግሥት ባልነበረበት ወቅት እንኳን የቀድሞው ሠራዊት አባላት መሣሪያ ይዘው ወርቅ ቤት በራፍ ላይ ቆመው ‹ወደ አገሬ መግቢያ መሳፈሪያ ስጡኝ› ይሉ እንደነበር እናስታውሳለን፡፡ ያኔ እንኳን ያልታየ በመሣሪያ የተደራጀ ዘረፋ ዛሬ መከሰቱ ወያኔ አዲስ አበባን መምራት አመቻሉን ብቻ ወያኔ ይዞብን የመጣው ባዕድ የዘራፊነት ባህል ቀስ በቀስ በማኅበረሰቡ ውስጥ እየገባ ባህላችንን እያበላሸ መሆኑን ያመለክታል" ብለዋል። ወ/ሮ ሶፊያ ከዲር የተባሉ የቤት እመቤት ደግሞ ‹‹መንግሥት ዘራፊ ሲሆን ተራ ሌቦችም ‹የአባትህ ቤት ሲዘረፍ አብረህ ዝረፍ› በሚል ብሄል ይበረታታሉ። ስለሆነም ጥፋቱ ራሱ ዘራፊ የሆነው መንግስት ነው›› ብለዋል፡፡

## በፓሪስ የስፖርት ፌስቲቫል ግንቦት 7 . . . ከገጽ 1 የዞረ

ግንቦት 7 ካቀዳቸው መርሀግብሮች መካካል ትልቅ ትኩረት ስቦ የነበረው የሙዚቃ ዝግጅቱ ሲሆን፣ አርብ እለት በርካታ ታዳሚዎች በተገኙበት እጅግ አስደሳች በሆነ መንገድ ቀርቧል።

በአገር ባህል ልብስ አጊጦ በመድረኩ ላይ ነግሶ ያመሸው ዝነኛው አርቲስት ሻምበል በላይነህ አገራዊ ስሜትን የሚነኩ ዜማዎችን ባቀረበበት ጊዜ፣ ወጣቶች የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ከፍ አድረገው በማውለብለብና የአገራቸውን ስም ደጋግመው በመጥራት ምሽቱን ያደመቁት ሲሆን አርቲስቱም ኢትዮጵያውያን አንድነታቸውን እንዲጠብቁና ከራሳቸው የግል ጥቅምና ፍላጎት ይልቅ የአገራቸውን ጥቅም እንዲያስቀድሙ ጠቃሚ ምክሮችን ሲለግስ አምሽቷል።

ታዳሚዎችም ሻምበል በላይነህ የወያኔን አገር የማፈራረስ ሥራ በመታገል በኩል እያሳየ ላለው ጽናት አድናቆታቸውን የገለጹ ሲሆን ድምጻዊውም በበኩሉ በምሽቱ ዝግጅት እጅግ መርካቱን ገልጿል። አንዳንድ የወያኔ ተላላኪዎችና የተንኮል ፖሊቲካ ባለሙያዎች ሻምበል በላይነህ ለግንቦት 7 ገቢ ማሰባሰቢያ ያቀረበውን የሙዚቃ ዝግጅት ለማደናቀፍ ጥረት አድረገው የነበረ ቢሆንም ድምጻዊው ግን ለቀረበበት ማስፈራሪያና ዛቻ ባለመበገር ዝግጅቱን በተሳካ ሁኔታ ለማቅረብ ችሏል።

ሻምበል በላይነህ አገራዊ አጀንዳን የያዘ አዲስ የሙዚቃ አልበም እየሰራ መሆኑን የገለጸልን ሲሆን በሚቀጥሉት ሶስት ወራትም ለሕዝብ ለማቅረብ ጥረት እንደሚያደርግ ተናግሯል።

የግንቦት 7 ወጣት አባላት ንቅናቄውን በማስተዋወቅ በኩል ያሳዩት ትጋት የብዙ ታዳሚዎችን ቀልብ ለመሳብ መቻሉን በቦታው ተገኝተው ዝግጅቱን የተከታተሉ ኢትዮጵያውያን ገልጸዋል።

## አባ ጳውሎስ "አዲስ ነገር" ጋዜጣ ስሜን አጠፋ ብለው ከሰሱ

የዘረኛ አምባገነኑ መለስ ዜናዊ ጉዳይ ፈጻሚ ሹመኛ እንደሆኑ የታወቀላቸው አባ ጳውሎስ "አዲስ ነገር" የተሰኘው ሣምንታዊ የአማርኛ ጋዜጣ ስሜን አጥፍቷል ብለው መክሰሳቸው ተዘገበ።

አባ ጳውሎስ ስሜን የሚያጠፋ ዘገባ አቅርቧል ብለው የከሰሱት የአዲስ ነገር ጋዜጠኛ አብርሀም በጊዜው እና የጋዜጣው ዋና አዘጋጅ መስፍን ነጋሽ በአራዳ ፓሊስ ጣቢያ ባለፈው አርብ ቃላቸውን ሰጥተው ዋስ ጠርተው መለቀቃቸው ታውቋል። ወያኔ ህጋዊ አሰራር የሚከተል ለማስመሰል አባ ጳውሎስ በጋዜጠኞቹ ላይ ክስ ከመመስረታቸው በፊት ጋዜጠኛ አብርሀም በጊዜው "ባልታወቁ ሰዎች" በጭካኔ መደብደቡ ይታወቃል። እነዚህ "ያልታወቁ ሰዎች" ጋዜጠኛውን "አንተ ነህ? የአባታችንን ስም የምታጠፋው?! አርፈህ ብትቀመጥ ይሻልሃል!!!" እያሉ በብረትና በድንጋይ ተዘግቧል።

አባ ጳውሎስም ‹‹መንግስት ከአድዋ ሆኖ ዳዳስ ከቡልጋ ይመጣል ብላችሁ አትጠብቁ›› ... "ልጄ (መለስ ዜናዊው የሚጠሩበት ቁልምጫ ነው) እስካለ ምንም ስለማልሆን አርፋችሁ አንገታችሁን ደፍታችሁ ብትኖሩ ይሻላል" እያሉ በግልጽ ለካህናት እና ለዳዳሳት እንደሚናገሩ ይታወቃል። **ይቀጥላል**

ከአስራ አምስት አመት በላይ በዘለቀው ስልጣናቸው ተደጋጋሚ ተቃውሞ ሲቀርብባቸው የቆየው አባ ጳውሎስ ሰሞኑን ተጋግሎ የነበረውን ቁጣ ለማብረድ ተቋዋሚዎቼ ናቸው ያሏቸው አባቶችን መኖሪያ ቤት በሮችን በወያኔ ወሮበሎች ማሰበራቸውና እንግልት እንዲፈጸምባቸው ማድረጋቸው አይዘነጋም።

## የወያኔ አመራሮች በከፍተኛ ተስፋ መቁረጥ እየተናጡ ነው ። አባይ-ጸሃዬ የኢትዮጵያ ህዝብ ደርግን ለመጣል የከፈለውን መሰዋዕትነት ጠቅልሎ ለትግራይ ልጆች ብቻ የሚያስረክብ ንግግር አደረገ

በ1993 በወያኔ በተሰነጠቀ ጊዜ ውህዳን ከሚባለው ቡድን ጋር አብሮ መለስን የከዳው እና የሀይል ሚዛኑ ወደ መለስ ማጋደሉን አይቶ "የዛሬን ማረኝ፤ ሁለተኛ እንዲህ ያለ ቅብጠት አይለምደኝም" ብሎ ለቅሶ በተቀላቀለበት ሁኔታ መለስን ለምኖ የተመለሰው አባይ ጸሀዬ፤ ባለፈው ቅዳሜ ለህወሀት አባላት ባደረገው ንግግር "ኢትዮድያዊያን የሰላም ፤የመረጋጋት እና የዴሞክራሲ ትሩፋቶችን እንዲያጣጥሙ" የትግራይ ልጆች ምትክ የሌለው የህይወት መሰዋትነት ከፍሎአል ሲል ላለፉት 18 አመታት በህወአት ጎጠኛ አገዛዝ ቁም ስቅሉን እያዩ ባለው ህዝባችን ላይ የሚያላግጥ ንግር አደረገ። በብሄራዊ የካርታ ስራ ድርጅት አዳራሽ "በ1960ዎቹ የነበሩት የትግራይ ወጣቶች እና የአሁኖቹ" በሚል ርእስ በተካሄደው ስብሰባ ላይ አባይ ጸሀዬ ደርግን ለማስወገድ በተደረገው ትግል ከህውሀት ውጪ ሌላ ማንም ሀይል እንዳልነበረ እና መስዋትነቱን ለብቻው የከፈለው ወያኔ እንደሆነ የሚገልጽ በዘረኝነት የተቃኘ ንግግር አቅርቧል። በስብሰባው ላይ ከትግራይ ተወላጅ ወጣቶች በስተቀር የሌላው ዘውጌ ወጣት ያልተገኘ መሆኑም ታውቋል።

አባይ ጸሐዬ በዘረኝነት የተለከፉትን ብጤዎቹን ለማስደሰት ዘረኛ ንግግሮችን ከማድረግ ባይቆጠብም መለስ በወያኔ ስንጠቃ ወቅት አባይ ከድቶት በነበረ ጊዜ የቋጠረበት ቂም አለቀቀውም ያሉት የውስጥ አዋቂ ምንጮች፤ እስካሁን ድረስ እንደማያነጋግረው እና ከሚኒስትርነቱ አውርዶ የብሄራዊ መረጃ እና የደህንነት አማካሪ ብሎ እንዳስቀመጠው ይጠቅሳሉ። አባይ ጸሀዬ ወያኔ ጫካ በነበረበት ጊዜ ከመለስ ዜናዊ እና ከስብሀት ነጋ ጋር አብሮ ትግራይን ለመገንጠል የተረቀቀውን ማኒፌስቶ እንዳዘጋጀ አይዘነጋም።

የወያኔ አመራሮች እና አባላት በተደጋጋሚ ሲናገሩ እንደሚደመጠው ደርግን ለመጣል በተካሄደው ትግል ከእነሱ ውጪ መስዋትነት የከፈለ ድርጅትም ሆነ ህዝብ እንደሌለ ነው። ከወያኔ ላልተናነሰ ጊዜ በጫካ ስለነበረው እና ስለታገለው ስለቀድሞ ኢህዲን የአሁኑ ብአዴን ተሳስተው እንኳን አለማውራታቸው የወያኔዎች ፍጹም ዘረኝነትን እና እብሪት ያሳያል ተብሎአል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተለየ ሁኔታ ወያኔ ደርግን ለመጣል የከፈለውን መስእዋትነት በእጅጉ አጋነው የሚያቀርቡ መጽሀፍት እና ፊልሞች መቅረባቸው ይታወቃል። እስካሁን የወያኔ ገድሎች በስፋት ላለመቅረባቸው ምክንያት ኢህዲን እንዳይሰማው ከሚል የመነጨ እንደሆነ እና የወያኔ ታሪክ በደንብ አለመተረኩ የትግራይ ህዝብ ለዚች ሀገር የከፈለው ወደር አልባ መስዋትነት የኢትዮድያ ብሄር እና ብሄረሰቦች እንዳያውቁት አድርጓል የሚል እምነት እንዳላቸው የወያኔ ታሪክ ጸሀፊዎች እየተናገሩ ነው።

ወያኔ በምርጫ ተወዳድሮ አሸንፎ የኢትዮድያ ህዝብን እንደማይመራ በተለይ ከግንቦት ሰባቱ ምርጫ በኋላ በደንብ ስለተረዳ ደርግን ለመጣል የከፈልኩት መስዋትነት በጣም ብዙ ስለሆነ ዘላለሜን እገዛችሓለሁ የሚል እጅግ ኋላቀር አስተሳቡን ለማስፋፋት መጽሀፍቱ እና ፊሌሞቹን እንደ አጋዥ የፕሮፓጋንዳ መሳሪያ ሳይጠቀምባቸው እንዳልቀረ ይገመታል።

ወያኔ በምርጫ 97 ተወዳድረው ያሸነፉትን ተመራጮች ወንድሜ የሞተበትን ትግል ስትቀማኝ ዝም ብዬ አላይም፤ በደም ያገኘሁትን ስልጣኔን በካርድ አላስረክብም እያለ በአደባባይ ይደነፋባቸው እንደነበረ ይታወሳል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**በ17870 KHZ በ 16 ሜትር ባንድ** እና **በ18350 KHZ በ19 ሜትር ባንድ** ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

**ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዣችንን እናቀርባለን።** g7radio@ginbot7.org